መልእክት ስድስት

## አጽናፍ-ዓለማዊው ታሪክ በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መሠረት—<br>አንዱን አዲሱን ሰው በእውነታ ማግኘት የሆነውን የጌታን የልብ መሻት ለማሟላት<br>መለኮታዊው ታሪክ በስብዕና ታሪክ ውስጥ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ኢዩ. 1፡4፤ 3፡11፤ ኤፌ. 1፡3-6፤ 2፡15፤ 4፡22-24፤ ሚክ. 5፡2፤ ራእ. 19፡7-9

**I. በዚህ አጽናፍ-ዓለም ሁለት ታሪኮች አሉ፤ የሰው ታሪክ፣ የስብዕና ታሪክ እና የእግዚአብሔር ታሪክ፣ መለኮታዊው ታሪክ፤ ፊተኛው እንደ ውጫዊ ቅርፊት ነው፣ ኋለኛው ደግሞ በቅርፊቱ ውስጥ እንዳለ ዘር ነው—ተዛ. ኢዩ. 1፡4፦**

ሀ. በስብዕና ታሪክ ውስጥ ያለው መለኮታዊው ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ዝርዝር ተገልጧል፤ የእግዚአብሔር ታሪክ ታሪካችን ነው ምክንያቱም እርሱ ከእኛ ጋር ተጣምሯል፦

1. ከሰው ጋር ለመጣመር ለሆነው እንቅስቃሴው ዝግጅት በጥንተ ዘላለም የሆነውን የእግዚአብሔርን ታሪክ ማየት ያስፈልገናል፦

ሀ. መለኮታዊው ታሪክ የጀመረው በዘላለማዊው አምላክና በኢኮኖሚው ነው፤ በኢኮኖሚው መሠረት እግዚአብሔር ከሰው ጋር አንድ ለመሆን፣ የሰው ሕይወት፣ የሕይወት አቅርቦትና ሁሉ ነገር ለመሆን እና ሰው እንደ መገለጡ እንዲኖረው ራሱን ወደ ሰው ውስጥ ለመሥራት ይፈልጋል—ኤፌ. 3፡9-10፤ 1፡10፤ ዘፍ. 1፡26፤ 2፡9።

ለ. ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ መከናወን የክርስቶስን ወሳኝ ሞት በተመለከተ ለመቁረጥ እግዚአብሔር በመለኮታዊ ሥላሴው በዘላለም ውስጥ ምክርን አደረገ—ሐዋ. 2፡23።

ሐ. ከመለኮታዊው ሥላሴ ሁለተኛው እንደ ሰው በቤተ ልሔም ለመወለድ ከዘላለም ወደ ጊዜ ውስጥ "አመጣጡን" ለማከናወን እየተዘጋጀ ነበር—ሚክ. 5፡2።

መ. እግዚአብሔር ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በክርስቶስ የሆኑትን አማኞች በመንፈሳዊ በረከቶች በሰማያዊ ስፍራ ባረካቸው—ኤፌ. 1፡3-6።

2. የእግዚአብሔር ታሪክ በሰው ውስጥ በተሠግዎ ጀመረ፣ በስብዕና ኑሮ፣ በስቅለት፣ በትንሣኤና በዕርገት ሂደቶቹም ቀጠለ፤ ሆሴዕ 11፡4 እነዚህ የሰው ገመዶች፣ የፍቅር እስራቶች እንደሆኑ ይናገራል፦

ሀ. መለኮታዊው ታሪክ፣ የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ በሰው ውስጥ፣ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ የመጨረሻ ፍጻሜን፣ ታላቋን አምላክ-ሰው፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ለማጠናቀቅ ለአዲሱ ሰው፣ እንደ መጀመሪያው ምሳሌ፣ በሂደት ካለፈው ክርስቶስ፣ ከአምላክ-ሰዉ ጋር ነው።

ለ. በክርስቶስ ተሠግዎና የስብዕና ኑሮ በኩል፣ የማይወሰነውን አምላክ ውሱን ወደሆነ ሰው ውስጥ አመጣው፣ ሦስታንዱን አምላክ ሦስት ክፍል ካለው ሰው ጋር አጣመረው አዋሐደውም፣ በብልጡግ ባሕሪያቱ የተትረፈረፈውን አምላክ በሚያውድ የስብዕና ሰናይ ባሕሪያት በኩል በስብዕናው ገለጠው።

ሐ. የክርስቶስ መስቀል የምትክ ሞት፣ ሁሉን-ያካተተ ሞት፣ አሮጌውን ፍጥረት ያስወገደና ችግሮችን ሁሉ የፈታ ሁሉን-ያካተተ ፍትሃዊ ቤዛነት ነበር (ዮሐ. 1፡29)፤ በመስቀሉ በእግዚአብሔር ተፈጥረው በኃጢአት የወደቁትን ነገሮች ሁሉ ዋጀ (ዕብ. 2፡9፤ ቆላ. 1፡20)፣ በመለኮታዊ ንጥረ-ነገሩ አዲሱን ሰው ፈጠረ (ጸነሰ) (ኤፌ. 2፡15)፣ መለኮታዊ ሕይወቱንም ከስብዕናው ቅርፊት ውስጥ ለቀቀው (ዮሐ. 12፡24፤ 19፡34፤ ሉቃ. 12፡49-50)።

መ. በትንሣኤው የእግዚአብሔር የበኩር ልጅ ለመሆን ተወለደ (ሐዋ. 13፡33፤ ሮሜ 1፡4፤ 8፡29)፣ ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ (1 ቆሮ. 15፡45)፣ እንደ የክርስቶስ አካል ክፍሎችና የአዲሱ ሰው፣ የቤተ ክርስቲያን ውቅሮች የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችን ዳግም ወለደ (1 ጴጥ. 1፡3፤ ቆላ. 3፡10-11)።

ሠ. ወደ ሰማያት ዐረገ ከዚያም ብዙዎች ለተካተቱበት ለሦስታንዱ አምላክ መገለጥ እንደ አንዱ አዲሱ ሰው ቤተ ክርስቲያንን ለማፍራት እንደ መንፈስ ወረደ—ኢዩ. 2፡28-32፤ ሐዋ. 2፡1-4፣ 16-21።

ለ. በመሆኑም ቤተ ክርስቲያን እንደ አንዱ አዲሱ ሰው እውነታ በውጫዊው የስብዕና ታሪክ ውስጥ ያለው የመለኮታዊው ምሥጢር ውስጠ-መሠረታዊ ታሪክ፣ የመለኮታዊው ታሪክም ክፍል ናት፤ በዚህ የመለኮታዊ ታሪክ የመጨረሻ ክፍል፣ ክርስቶስ የክርስቶስ ተቃዋሚውንና ሠራዊቱን ለማሸነፍ እንደ ሠራዊቱ ከድል-ነሺዎቹ ጋር ተመልሶ ይመጣል (ኢዩ. 1፡4፤ 3፡11)።

ሐ. ይህን ተከትሎ የሺሁ-ዓመት መንግሥት ይመጣል፤ በመጨረሻም ይህ መንግሥት በአዲሱ ሰማይና በአዲሱ ምድር፣ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ይጠናቀቃል፤ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ታሪክ የመጨረሻውና ምርጡ፣ የማጠናቀቂያው ደረጃ ትሆናለች።

**II. ከጴጥሮስ (የማጥመድ አገልግሎት)፣ ከጳውሎስ (የግንባታ አገልግሎት) እና ከዮሐንስ (የመጠገን አገልግሎት)፣ አንዱን አዲሱን ሰው ለማግኘት የሆነውን የጌታን የልብ መሻት ማየት እንችላለን፦**

ሀ. እግዚአብሔር በበዓለ ኀምሳ ቀን ብዙ አይሁድ አማኞችን ለማምጣት ጴጥሮስን ተጠቀመ (ሐዋ. 2፡5-11)፤ በተጨማሪም ቆርኔሌዎስ በጸሎት ራእይን ተቀበለ (10፡30)፣ ጴጥሮስም በጸሎት ራእይን ተቀበለ (ቁ. 17፣ 19) በዚህም በኩል ለአንዱ አዲስ ሰው ተግባራዊ ሕልውና አሕዛብ ይገኙ ዘንድ የእግዚአብሔር እቅድና እንቅስቃሴ (ቁ. 9-14፣ 27-29) ተከናውኗል።

ሰ. ጳውሎስ በኤፌሶን 2፡14-15 አዲስ-ሰው-በሚፈጥር ሞቱ በኩል ክርስቶስ አይሁድንም አሕዛብንም ወደ አንድ አዲስ ሰው ውስጥ እንደፈጠራቸው ገልጧል (ተዛ. 4፡22-24)፤ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13 "አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን" እኛ ሁላችን ወደ አንድ አካል ውስጥ እንደተጠመቅን ይነግረናል፤ በገላትያ 3፡27-28 ጳውሎስ ወደ ክርስቶስ ውስጥ የተጠመቁት እነዚያ ክርስቶስን እንደለበሱትና "በዚያ አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው [ሊኖር እንደማይችል]" ይነግረናል፤ በቆላስይስ 3፡10-11 ጳውሎስ አይሁድና ግሪክ በአዲሱ ሰው ውስጥ ስፍራ እንደሌላቸው ይነግረናል።

ሐ. ዮሐንስ ጌታ "ሰዎችን ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ" (ራእ. 5፡9) በደሙ እንደዋጀ ይነግረናል፤ እነዚህ የተዋጁት እንደ አንዱ አዲሱ ሰው ቤተ ክርስቲያንን ያዋቅራሉ፤ በዮሐንስ በኩል አብያተ ክርስቲያናት ወርቃማ መቅረዞች እንደሆኑ (1፡11-12)፣ በመጠናቀቂያውም እነዚህ መቅረዞች አዲሲቱ ኢየሩሳሌም እንደሚሆኑ ደግሞ እናያለን፤ በመቅረዞቹ ውስጥና በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም በሰዎች ልዩነቶች እንደሌሉ ማየት እንችላለን።

መ. ይህ ሁሉ አንዱን አዲሱን ሰው በእውነታ ለማግኘት (ኤፌ. 4፡22-24) ለሆነው ለጌታ የልብ መሻት መከናወን በተግባራዊ የየዕለት ሕይወታችን ፈርጆች ሁሉ በአእምሯችን መንፈስ እንታደስ ዘንድ ከአንዱ መንፈስ በመጠጣት (1ቆሮ. 12፡13) በየዕለቱ አሮጌውን ሰው እያወለቅን አዲሱን ሰው መልበስ እንደሚያስፈልገን ያመለክታል።

**III. ከመለኮታዊው ታሪክ ጋር አዲሱ ፍጥረት አለ—አዲሱ ሰው ከአዲስ ልብ፣ አዲስ መንፈስ፣ አዲስ ሕይወት፣ አዲስ ባሕሪይ፣ አዲስ ታሪክና አዲስ መጠናቀቅ ጋር—[ከእንግሊዝኛው መዝሙር መጽሐፍ] መዝሙር #16፤ ሕዝ. 36፡26፤ 2ቆሮ. 3፡16፤ ማቴ. 5፡8፤ ቲቶ 3፡5፦**

ሀ. መለኮታዊው ታሪክ፣ የእግዚአብሔር ታሪክ በሰው ውስጥ፣ ከክርስቶስ ተሠግዎ ሕይወት-የሚሰጥ መንፈስ ለመሆን እስካለው ዕርገቱ ነበር፣ ከዚያም እኛን ወደ አንዱ አዲስ ሰው ሙሉ እውነታ ውስጥ ለማምጣትና የክርስቶስ ክብርት ሙሽራ ለማድረግ በእግዚአብሔር ዳግም የመውለድ፣ የመቀደስ፣ የማደስ፣ የመለወጥ፣ የማስመሰልና የማክበር ሕይወታዊ ማዳን በኩል በእኛ በማደሩ ቀጥሏል—ኤፌ. 4፡22-24፤ ሮሜ 5፡10፤ ራእ. 19፡7-9።

ለ. አሁን ይህን ጥያቄ ራሳችንን መጠየቅ ያስፈልገናል፦ በመለኮታዊው ታሪክ ውስጥ እየኖርን ነው፣ ወይስ እንዲያው በሰው ታሪክ ውስጥ ብቻ እየኖርን ነው?

1. ሁላችንም በሰው ታሪክ ውስጥ ተወልደናል፣ ነገር ግን በመለኮታዊው ታሪክ ውስጥ እንደገና ተወልደናል፣ ዳግም ተወልደናል፤ ኑሯችን በዓለም ውስጥ ከሆነ፣ በሰው ታሪክ ውስጥ እየኖርን ነው፤ ነገር ግን እንደ አንዱ አዲሱ ሰው እውነታ በቤተ ክርስቲያን እየኖርን ከሆነ፣ በመለኮታዊው ታሪክ ውስጥ እየኖርን ነው፤ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት የእግዚአብሔር ታሪክ የእኛ ታሪክ ነው፤ አሁን ሁለት ወገኖች—እግዚአብሔር እና እኛ—አንድ ታሪክ፣ መለኮታዊው ታሪክ አለን።
2. ድል-ነሺ ሙሽራው ለመሆን አንዱን አዲሱን ሰው በእውነታ እንድንሆን ለሕይወታዊ መዳናችንና የሠላም ወንጌል በምድር ሁሉ በመሰበኩ በኩል (ኤፌ. 2፡14-17፤ 6፡15፤ ተዛ. ማቴ. 24፡14) ለእርሱ መሰራጨት ምሥጢራዊዎቹን፣ መለኮታዊዎቹን ነገሮች እየተለማመድንና እየተደሰትን በመለኮታዊው ታሪክ ውስጥ ስላለን ጌታ ይመስገን።

© 2020 Living Stream Ministry